የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፰
አዲስ አበባ — የካቲት ፮ ቀን ፲፱፻፹፰

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

2nd Year No. 8
ADDIS ABABA – 13th February, 1996

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፳/፲፱፻፹፰ ዓ.ም.
የቱኒዚያ ሪፐብሊክ የኢኮኖሚ ፡ የሳይንስ ፡ የባህልና የቴክኒክ ትብብር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ .................. ገጽ ፻፲፫

CONTENTS

Proclamation No. 20/1996
Republic of Tunisia Agreement on Economic, Scientific, Cultural and Technical Cooperation Ratification Proclamation ............................................. Page 113

## አዋጅ ቁጥር ፳/፲፱፻፹፰

## ከቱኒዚያ ሪፐብሊክ መንግሥት ጋር የተደረገውን የትብብር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥትና የቱኒዚያ ሪፐብሊክ መንግሥት በኢኮኖሚ ፡ በሳይንስ ፡ በባሕልና በቴክኒክ መስኮች በሚቻለው መጠን ሁሉ ትብብር ለማድረግ ትብብሩንም ለማስፋፋት ባላቸው ፍላጎት እንዲሁም የትብብር ግንኙነቱ የሚያስገኘውን የጋራ ጠቀሜታ በማገናዘብ ፡ በሁለቱ ሀገሮች መካከል በቱኒዚያ ሪፐብሊክ ዋና ከተማ በቱኒዝ ጥቅምት ፳፬ ቀን ፲፱፻፹፯ የትብብር ስምምነት በመፈረሙ ፤

ስምምነቱ በቍርጥ ሥራ ላይ የሚውለው ሥልጣኑ ባላቸው የሁለቱ ሀገሮች የመንግሥት አካላት መጽደቁን ከ የሚያረጋግጡ ሰነዶች ልውውጥ ከሚደረግበት ቀን ጀምሮ እንደሚሆን በስምምነቱ ውስጥ ስለተመለከተ ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የካቲት ፮ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ ፤

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት ከዚህ እንደሚከተለው ታውጇል ።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የቱኒዚያ ሪፐብሊክ የኢኮኖሚ ፡ የሳይንስ ፡ የባሕልና የቴክኒክ ትብብር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፳/፲፱፻፹፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

## PROCLAMATION NO. 20/1996

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE COOPERATION AGREEMENT WITH THE GOVERNMENT OF THE REPUBLIC OF TUNISIA

WHEREAS, the Transitional Government of Ethiopia and the Government of the Republic of Tunisia, desirous of promoting and enlarging economic, scientific, cultural and technical coopertion between their two countries to the greatest possible extent, and mindful of advantages to be mutually derived from such cooperation, had signed a Cooperation Agreement in Tunis on the 3rd day of November, 1994;

WHEREAS, it is stipulated in the Agreement that the Agreement shall definitively enter into force on the date of exchange of notes confirming its approval by competent authorities of each country;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Agreement at its session held on the 13th day of February, 1996;

NOW, Therefore, in accordance with Article 55 sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Republic of Tunisia Agreement on Economic, Scientific, Cultural and Technical Cooperation Ratification Proclamation No. 20/1996".

ያንዱ ዋጋ
Unit Price } 1·20

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፪· <u>ስምምነቱ ስለ መጽደቁ</u>

በኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥትና በቱኒዚያ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል ጥቅምት ፳፬ ቀን ፲፱፻፹፯ ቱኒዝ ከተማ ላይ የተፈረመው የኢኮኖሚ ፣ የሳይንስ ፣ የባሕልና የቴክኒክ ትብብር ስምምነት ፀድቋል ።

፫· <u>የሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካላት ሥልጣን</u>

በስምምነቱ የተካተቱት የትብብር መስኮች የሚመለከቷቸው የፌዴራሉ አስፈጻሚ አካላት በየስራ መስካቸው ስምምነቱ በስራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቷቸዋል ።

፬· <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከየካቲት ፭ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ·ም· ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ የካቲት ፭ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ·ም·

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

2. *Ratification of the Agreement*

The Agreement on Economic, Scientific Cultural and Technical Cooperation signed in Tunis on the 3rd day of November, 1994 between the Transitional Government of Ethiopia and the Government of the Republic of Tunisia is ratified.

3. *Power of Concerned Executive Organs*

Federal Executive Organs concerned with the fields of cooperation included in the Agreement are hereby empowered to implement the Agreement with regard to their respective fields of activity.

4. *Effective date*

This Proclamation shall enter into force as of the 13th day of February, 1996.

Done at Addis Ababa, this 13th day of February, 1996

NEGASO GIDADA (DR.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE